## መግቢያ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) በዘር፣ በኃይማኖት በቋንቋ በፆታና በሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መመዘኛዎች በዜጎች መካከል ልዩነት ሳያደርግ በማደራጀት የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ይታገላል፡፡ የፓርቲውን ራዕይ እውን ለማድረግ፣ ዓላማውን ከግብ ለማድረስና እቅዶቹን ለመተግበር አባላቱ የሚመሩበትና የሚገዙበት የመተዳደሪያ ደንብ አስፈላጊ ነው፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡ በፓርቲው የተለያዩ አካላትና አባላት መካከል ጤናማና ዴሞክራሲያዊ የሥራ ግንኙነት እንዲሁም የዓላማና የተግባር አንድነት ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ደንቡ የፓርቲው አባላት መብትና ግዴታቸውን አውቀው በፓርቲው ጉዳዮች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ከማስቻሉም በላይ በግልጽነትና ተጠያቂነት  መርህ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ የአሠራር ባህልን ለማዳበር ይረዳል፡፡ በፓርቲው የተለያዩ አካላትና የአመራር አባላት መካከል ግልጽ የሆነ የሥራ ክፍፍልና ግን ኙነት  በመፍጠር  የፓርቲውን አሠራር አስተማማኝና ቀልጣፋ ለማድረግ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ይህን የመተዳደሪያ ደንብ አጽድቋል፡፡

# ክፍል አንድ
# አጠቃላይ

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ፤**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ «የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) መተዳደሪያ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2. የፓርቲው ስያሜ፤**

የፓርቲው ስያሜ «አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ » ሲሆን በአጭሩ «አንድነት» ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 3. የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት፤**

የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይኖሩታል፡፡

**አንቀጽ 4. ዋና ዋና ድርጅታዊ የአሰራር መርሆች፤**

የፓርቲው አባላትና የአመራር አካላት የሚከተሉትን ድርጅታዊ የአሰራር መርሆች ያከብራሉ፡፡

4.1 በፓርቲው የተለያዩ አካላትና የአመራር አባላት መካከል የሥራ ክፍፍል ሥርዓትን በመፍጠር፣ የክትትልና የቁጥጥር ስልቶችን በመዘርጋት በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆች ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ የአሠራር ባህልን ማዳበር፣

4.2 የፓርቲው አባላትና የአመራር አካላት መብትና ግዴታቸውን ጠንቅቀው በማወቅና የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በማክበርና በማስከበር በፓርቲው ውስጥ የህግ የበላይነትን ማስፈን፣

4.3 የፓርቲውን መሠረታዊ ዓላማዎች፣ የፖሊሲ አቅጣጫዎችና የትግል ስልቶች በመገንዘብ በተጨባጭ መረጃና በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ አቋም ማራመድ፣

4.4 በፓርቲው ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የማንሸራሸር መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ለብዙሃን ውሳኔ ተገዥ መሆንና የፓርቲውን መዋቅር ጠብቀው የሚተላለፉ የበላይ አካላትን ውሳኔና መመሪያዎች ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ፣

4.5 አሉባልታን፣ ሥርዓትና ደንብን ያልተከተለ አሠራርን፣ የግለሰብ ፈላጭ ቆራጭነትንና አፍራሽ ቡድናዊነትን መታገል፡፡

**አንቀጽ 5. አባልነት፤**

**5.1 እጩ አባል**

**5.1.1** ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ[1]፣ በፖለቲካ ለመሳተፍ በህግ ገደብ ያልተጣለበት፣ የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፣ የፓርቲውን ዓላማዎችና እምነቶች የተቀበለና ለተግባራዊነታቸውም ለመታገል ዝግጁ የሆነ፣

**5.1.2** የፓርቲውን መዋጮ ለመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆነ፣

**5.1.3** በዘር፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፆታ፣ በቀለም፣ ወይም በማንኛውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መመዘኛ በኢትዮጵያውያን መካከል ልዩነት የማያደርግ፣

**5.1.4** የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና የበላይነት የሚቀበልና በአገሪቱ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ለመታገል የወሰነ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፓርቲው አባል ለመሆን ሲጠይቅ በእጩ አባልነት ይመዘገባል::

**5.2 ሙሉ አባል፤**

**5.2.1** ከፓርቲው መሥራች ጉባኤ በፊት የተመዘገቡና በመሥራች አባልነት ዝርዝራቸው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተላለፈ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የፓርቲው መሥራች አባላት ናቸው::

**5.2.2** የፓርቲው እጩ አባል ሆኖ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ እስከ ሦስተኛው ወር መጨረሻ ድረስ የዲስፕሊን ግድፈት ያልተገኘበትና የእጩ አባልነት ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ ዕጩ አባል፣ የአባልነት ጥያቄው በሁለት ሙሉ አባላት ከተደገፈ የፓርቲው ሙሉ አባል ይሆናል::

**5.2.3** በፓርቲው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠይቆ አባል ለመሆን ፈቃደኝነቱን የገለፀ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ መሠረት በአንቀጽ 5.2.2 የተመለከተው ተፈፃሚ ሳይሆን የፓርቲው ሙሉ አባል ሊሆን ይችላል::

**5.3 ተባባሪ አባል፤**

**5.3.1** በፓርቲው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የግል ሁኔታቸው የማይፈቅድላቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ የፓርቲው ተባባሪ አባል ሊሆኑ ይችላሉ::

**5.3.2** ተባባሪ አባላት ለፓርቲ ኃላፊነት ቦታ ለመምረጥ እና ለመመረጥ እንዲሁም በፓርቲው ውሳኔዎች ላይ ድምጽ ለመስጠት ካለመቻል በስተቀር ሌሎች የአባልነት መብቶች ሁሉ ይኖሯቸዋል::

**አንቀጽ 6. የአባልነት መብት፤**

**6.1 ማንኛውም አባል:-**

**6.1.1** በፓርቲው ስብሰባዎች ሃሳብ የማቅረብና ድምጽ የመስጠት፣

---

[1] በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለፀ ለሴት ፆታም የሚያገለግል ነው::

6.1.2 የመምረጥና የመመረጥ፣

6.1.3 የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም መከበሩን የመከታተል፣

6.1.4 በራስ ተነሳሽነት አዳዲስና ጠቃሚ ሃሳቦችን የማፍለቅ፣ ለፓርቲ አመራር የማስተላለፍ፣ በፓርቲ እንቅስቃሴዎችና ተግባሮች የመሳተፍ፣

6.1.5 ድርጅታዊ መዋቅርን ጠብቆ ስለፓርቲው አሠራር ማብራሪያና መረጃ የመጠየቅና ሂስ የማቅረብ መብት አለው::

6.1.6 ማንኛውም አባል በራሱ ፍላጎት አባልነቱን መተው ይችላል::

6.2 ማንኛውም ዕጩ አባል በፓርቲው የተለየዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት አለው:: ሆኖም የመምረጥ የመመረጥና የፓርቲ ውሳኔዎች ላይ ድምጽ የመስጠት መብት የለውም::

## አንቀጽ 7. የአባልነት ግዴታ፤

7.1 የፓርቲውን ዓላማና ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ፣ ለህዝብ ማስተዋወቅና ማሰራጨት፣

7.2 የፓርቲውን ደንብና የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ማክበርና የፓርቲውን አመራር ውሳኔ ዎች ተግባራዊ ማድረግ፣

7.3 በተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችና፣ ፓርቲው በሚጠራቸው የተለያዩ ስብሰባዎች መሳተፍ፣

7.4 የአባልነት መዋጮን በወቅቱ መክፈልና በፓርቲው የገንዘብ መዋጮ ተግባራት መሳተፍ፣

7.5 የፓርቲውን ዓላማ፣ አንድነትና አሠራር ከሚጎዱ ማናቸውም እንቅስቃሴዎችና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች መቆጠብ፣

7.6 ለፓርቲው ታማኝ መሆንና ሚስጥር መጠበቅ፣

## አንቀጽ 8. አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች፤

አንድ የፓርቲ አባል አባልነቱ ሊቋረጥ የሚችለው:-

8.1 በራሱ ፍላጎት አባልነቱ እንዲቋረጥ ጥያቄ በጽሑፍ ሲያቀርብ፣ ወይም

8.2 በሞት ሲለይ ወይም በህግ ችሎታ ሲያጣ፣ ወይም

8.3 በዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ሥልጣን ባለው አካል ከአባልነት እንዲወገድ ሲወሰን ነው::

# ክፍል ሁለት
# ድርጅታዊ መዋቅር

**አንቀጽ 9. <u>የፓርቲው አካላት፤</u>**

ፓርቲው የሚከተሉት የድርጅት አካላት ይኖሩታል፡፡

9.1 ጠቅላላ ጉባዔ፣

9.2 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ፣

9.3 ብሔራዊ ምክር ቤት፣

9.4 ብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

9.5 የዞን ምክር ቤት፣

9.6 የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

9.7 የወረዳ ምክር ቤት፣

9.8 የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

9.9 የመሠረታዊ ድርጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

9.10 ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፡፡

**አንቀጽ 10. ጠቅላላ ጉባዔ፤**

10.1 የጠቅላላ ጉባዔ አባላት

10.1.1 የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤትና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት፣

10.1.2 ፓርቲው መዋቅሩን ከዘረጋባቸው ወረዳዎች በየወረዳው ም/ቤት የሚመረጥ አንዳንድ አባል፣

10.1.3 ከእያንዳንዱ ዞን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ወይም እንደሁኔታው የዞን አስተባባሪ ኮሚቴውን የሚወክል አንድ አባል፣

10.1.4 በውጭ ሀገር ከሚገኙ የፓርቲው ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎች የሚወከሉ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ድምጽ የማይሰጡ ተሳታፊዎች፣

10.1.5 በተለያዩ መንገዶች ለፓርቲው የጎላ አስተዋጽኦና ድጋፍ ከአደረጉና ለጠቅላላ ጉባዔ አባልነት የሚያበቃ ውክልና ካላገኙ አባላት መካከል በብሔራዊ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚመረጡ እስከ 25 የሚደርሱ አባላት ፣

10.1.6 ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጠቅላላ ጉባኤውን ውክልና ዴሞክራሲያዊና ፍትሀዊ ለማድረግ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት በተሳታፊዎች ቁጥርና አካባቢያዊ ውክልና ላይ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፣

10.1.7 በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የሴቶችና የወጣቶች[2] ተመጣጣኝ ተሳትፎ እንዲኖር ጥረት ይደረጋል፣

10.1.8 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን በሚጓደሉበት ጊዜ ብሔራዊ ም/ቤቱ ቁጥሩን ሊያሟላው ወይም እንዳስፈላጊነቱ ሊቀንሰውና ሊጨምረው ይችላል::

10.1.9 የፓርቲው የመጀመሪያ ጠ/ጉባኤ አባላት አመራረጥ የፓርቲው አስተባባሪ ኮሚቴ በሚወስነው መሠረት የሚፈፀም ይሆናል::

## 10.2 የጠቅላላ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር፤

የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ በየሦስት ዓመቱ የሚሰበሰብና የፓርቲው ከፍተኛው የሥልጣን አካል ሲሆን፣

10.2.1 የፓርቲውን ስያሜ፣ ዓርማ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ፕሮግራም፣ ደንብና ፖሊሲዎች ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይሽራል፣

10.2.2 አምስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ በመሰየም፣የብሔራዊ ምክር ቤትና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፣

10.2.3 ከብሔራዊ ምክር ቤትና ከኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን የሚቀርቡለትን የሥራ ክንውን ሪፖርቶች እየመረመረ ያፀድቃል፣ ውሳኔዎች ይሰጣል፣

10.2.4 ፓርቲውን በሚመለከቱ በማናቸውም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል፣

10.2.5 ጠቅላላ ጉባዔው ከሥልጣኑ ቀንሶ ለብሔራዊ ምክር ቤት በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

## አንቀጽ 11. የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት፤

ብሔራዊ ምክር ቤቱ ከጠቅላላ ጉባኤው ቀጥሎ ከፍተኛው የፓርቲው የሥልጣን አካል ሲሆን በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ 60 ቋሚና 15 ተለዋጭ አባላት ይኖሩታል:: ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ:-

11.1 የፓርቲውን ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቃነመናብርት፣ ዋና ፀሐፊና ሌሎች ብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሎችን ይመርጣል፤ የዲሲፕሊን ጉድለት መፈፀማቸው አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ በ2/3ኛ ድምጽ በመሻር በቦታቸው ከብሔራዊ ምክር ቤት አባላት መካከል ሌላ መምረጥ ይችላል፣

11.2 የብሔራዊ ምክር ቤቱን ስብሰባ የሚመራ ሰብሳቢና ቃለ ጉባኤ የሚይዝ ፀሐፊ ከመካከሉ ይመርጣል:: ኃላፊነትና ተግባራቸው ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል::

---

[2] ወጣት የሚባለው ከ18 - 29 ዓመት ባለው የእድሜ ክልል የሚገኝ ነው::

11.3 በጠቅላላ ጉባዔው የፀደቁ ፖሊሲዎችን እንዲሁም ሌሎች ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

11.4 የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት የዲስፒሊን ጉድለት መፈፀማቸው አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምጽ እነሱን በመሻር በቦታቸው ከብሔራዊ ምክር ቤት ተለዋጭ አባላት መካከል በአገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሠረት መተካት ይችላል።

11.5 የጠቅላላ ጉባዔውን መደበኛ፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴን ያቋቁማል፣

11.6 ስለፓርቲው የሥራ ክንውን ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል፣

11.7 በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚቀርብለትን የፓርቲውን የሥራ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣

11.8 የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ሥራ ይገመግማል፣ የፀደቀው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

11.9 ይህን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አድርጎ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድን፣ የገንዘብና የንብረት አስተዳደርን፣ የጽ/ቤቱን ቋሚ ሠራተኞች አስተዳደርን እና ሌሎች የተለያዩ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

11.10 ፓርቲው ከመሠልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚመሠርታቸውን ከህብረት እስከ ውህደት የሚደርሱ የትግል ግንኙነቶችን በተመለከተ ስምምነት ይፈጽማል። ይህንኑም ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል።

11.11 ከመሠልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በሚፈጠሩ የውህደት ስምምነቶች ላይ ተመስርቶ የምክር ቤቱን አባላት ብዛት በጊዜያዊነት እስከ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ድረስ እንደአስፈላጊነቱ ከፍ ሊያደርገው ይችላል፣

11.12 ቋሚ የም/ቤቱ አባላት ለረጅም ጊዜ መሳተፍ የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ከተለዋጭ አባላቱ መካከል ባላቸው የድምጽ ብልጫ ቅደም ተከተል መሠረት እነሱን ተክተው እንዲሰሩ ያደርጋል፣

11.13 ፓርቲውን በመወከል በየደረጃው በምርጫ የሚወዳደሩ አባሎች ዝርዝር በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲቀርብለት ያፀድቃል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፣

11.14 የፓርቲው ፕሮግራም ፣ደንብ ፣ዓርማ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር እንዲዘጋጅ ወይም እንዲሻሻል በማድረግ ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ያፀድቃል፣

11.15 ከጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

11.16 ም/ቤቱ ከሥልጣኑ ከፊሉን ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

11.17 የብሔራዊ ምክር ቤቱ አባላት በድጋሚ ካልተመረጡ በስተቀር የአንድ ዙር የሥራ ጊዜያቸው ለሦስት ዓመት ብቻ ይሆናል።

አንቀጽ 12. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ፤

ሰባት ሙያና ብቃት ያላቸው አባላት ያሉት የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን በጠቅላላ ጉባዔ ይቋቋማል:: ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

12.1 መተዳደሪያ ደንቡን ይተረጉማል፣ በፓርቲው የሚወጡ መመሪያዎች ከደንቡ ጋር መጣጣማቸውንና በተግባር ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል::

12.2 የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

12.3 በብሔራዊ ም/ቤቱ የማይታረሙ ስህተቶች ሲፈጠሩ 1/3ኛ የጠቅላላ ጉባዔ አባሎችን የድጋፍ ፊርማ በማሰባሰብ የጠቅላላ ጉባኤው እንዲጠራና ጉድለቶቹ እንዲታረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል:: በዚህም መሠረት ብሔራዊ ም/ቤቱ በሦስት ወራት ውስጥ ጠ/ጉባኤውን መጥራት ካልቻለ ኮሚሽኑ ጠቅላላ ጉባኤውን ሊጠራ ይችላል፣

12.4 ለጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ያቀርባል፣ ለተከሰቱ ችግሮችም የመፍትሔ ሃሳቦችን ያቀርባል፣

12.5 በፓርቲው ውስጥ የሚከሰቱ የአባላትም ሆነ የአመራር አካላት የሥነ ሥርዓት ጉዳዮችን ይግባኝ በመስማት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

12.6 ከአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና ጥቆማዎችን መሠረት በማድረግ የአሠራር ጉድለቶች በወቅቱ እንዲታረሙና ችግሮችም እንዲፈቱ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፣

12.7 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን መዋቅሩን እስከታች ድረስ ሊዘረጋና የራሱን የሥራ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

12.8 በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

12.9 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት የሥራ ዘመን በድጋሜ ካልተመረጡ በስተቀር ሦስት ዓመት ይሆናል፣

አንቀጽ 13፡ ብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤

የብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ም/ቤት ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት አባላት አሉት::

13.1 የፓርቲው ሊቀመንበር፣

13.2 ምክትል ሊቀመንበርና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ፣

13.3 ምክትል ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ፣

13.4 ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ ፣

13.5 ምክትል ሊቀመንበርና የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ፣

13.6 ዋና ፀሐፊ፣

13.7 ምክትል ፀሐፊ፣

13.8 የጥናትና ምርምር ጉዳይ ኃላፊ፣

13.9 የሕግና ሥነ-ሥርዓት ጉዳይ ኃላፊ፣

13.10 የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ፣

13.11 የዕቅድና ስትራቴጂ ጉዳይ ኃላፊ፣

13.12 የማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ፣

13.13 የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣

13.14 የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ፣

13.15 ምክትል የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

13.16 ምክትል የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፣

13.17 ምክትል የህዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ፣

13.18 ምክትል የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ፣

**አንቀጽ 14. የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፤**

ብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ሆኖ፣

14.1 ከሊቀመንበሩ፣ ም/ሊቃነመናብርቱና ከዋና ፀሐፊው ቀጥሎ ያሉ የሥራ ኃላፊነቶችን ድልድል ያከናውናል:: ይህንንም ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ያሳውቃል:: እያንዳንዱ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ኃላፊነቱን በብቃት፣ በታማኝነት፣ በግልጽነትና በተጠያቂነት መወጣቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

14.2 በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የሚመሩ ቋሚ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ የቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢዎችን ይመድባል፣ ሌሎች የቋሚ ኮሚቴ አባላትንም ይደለድላል::

14.3 እንደ አስፈላጊነቱ ለፓርቲው ሥራ ጊዜያዊ ግብረ-ኃይሎችን ሊያቋቁምና ተልዕኳቸውን ሲጨርሱም ሊያፈርሳቸው ይችላል፣

14.4 የሥራ አስፈፃሚና የቋሚ ኮሚቴ አባላት ፓርቲውን በሚጎዳ ተግባር ላይ ተሰማርተው ከተ ገኙ የሥነ-ሥርዓት ክስ እስከሚመሠረትባቸው ድረስ ተጨባጭ ማስረጃን መሠረት በማድረግ በ2/3ኛ ድምጽ ከኃላፊነት ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ አግዶ ሊያቆያቸው ይችላል፣

14.5 የፓርቲውን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ም/ቤቱ በማቅረብ ያፀድቃል::

14.6 የፓርቲውን ሂሳብ የሚያንቀሳቅሱ ሰዎችን ከብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና እንደ አስፈላጊነቱ ከብሔራዊ ምክር ቤቱ አባላት መካከል ይወክላል:: በየደረጃው የሚወቀሩ የፓርቲው አካላትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ሂሳብ ከፍተው እንዲያንቀሳቅሱ ሊወክል ይችላል::

14.7 የብሔራዊ ም/ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ያውላል::

14.8 የብሔራዊ ም/ቤቱን መደበኛ፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል:: ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ሰብሳቢም አጀንዳዎቹን አስቀድሞ ያሳውቃል::

14.9 ስለ ሥራ እንቅስቃሴው በየሦስት ወሩ ለብሔራዊ ም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

14.10 ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሊኖር የሚገባን የትግል ግንኙነት በተመለከተ የብሔራዊ ም/ቤቱን ውሳኔና መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፣

14.11 ከሥልጣኑ ከፊሉን ለሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎችና ለሌሎች የሥልጣን አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

14.12 በእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የሥራ እቅድና የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፣

14.13 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ሲጓደል ከብሔራዊ ም/ቤቱ አባላት መካከል በመተካት በብሔራዊ ም/ቤቱ እንዲፀድቅ ያደርጋል::

14.14 እንደ አስፈላጊነቱ ብሔራዊ ም/ቤቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ቁጥር ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርገው ይችላል

14.15 ከብሔራዊ ም/ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣
ያፀድቃል፣

14.16 የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በድጋሚ ካልተመረጡ በስተቀር የአንድ ዙር የስራ ጊዜያቸው ሦስት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም ግን በሊቀመንበርነት፣ በም/ሊቀመንበ ርነትና በፀሐፊነት የኃላፊነት ቦታ ማገልገል የሚቻለው ለሁለት ተከታታይ ዙሮች ብቻ ነው::[3] ሆኖም ከአንድ የሥራ ዘመን እረፍት በኋላ ተመልሶ ለዚያው ቦታ ሊመረጥ ይችላል::

## አንቀጽ 15. የዞን ምክር ቤት ፣

የዞን ምክር ቤት የሚቋቋመው የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት በአንድ አካባቢ የዞን ምክር ቤት ለማቋቋም አስፈላጊ ሁኔታዎች ተሟልተዋል ብሎ ሲያምን ሲሆን፣ የምክር ቤቱ አባላት የሚከተሉት ናቸው:-

15.1 በዞኑ ሥር ካሉ ከእያንዳንዱ ወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች የሚወከሉ ከ1-3 አባላት፣ ይኖራሉ፣

15.2 በተለያዩ መንገዶች ለፓርቲው የጎላ አስተዋጽኦና ድጋፍ ካደረጉና በፓርቲ መዋቅር መሠረት ካልተመረጡ አባሎች መካከል በዞኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚመረጡ አምስት አባላት ይሆናሉ፣

15.3 በዞኑ ም/ቤት ውስጥ የሴቶችና ወጣቶች ተመጣጣኝ ተሳትፎ እንዲኖር ጥረት ይደረጋል::

15.4 የዞን ምክር ቤት ስብሰባ በአመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል:: ሆኖም ስብሰባው መካሄድ ያለበት የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ከሚካሄድበት ጊዜ በፊት በአሉት ሁለት ወራት ውስጥ መሆን አለበት፣

15.5 የዞን ምክር ቤት አባላት በድጋሚ ካልተመረጡ በስተቀር የአንድ ዙር የሥራ ዘመናቸው ሦስት ዓመት ነው::

---

[3] ነገር ግን ለሁለት ዙር ከያዘው የኃላፊነት ቦታ ውጭ ለሌሎች የኃላፊነት ቦታዎች ሊመረጥ ይችላል::

**አንቀጽ 16፡ የዞን ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር፣**

የዞን ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለፓርቲው ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ፣

የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፣

የዞኑን ልዩ ሁኔታ በማጥናት የፓርቲውን እንቅስቃሴ ለማጠናከር በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን ይሰጣል፣ በተግባር መተርጎማቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

የዞኑን የሥራና የበጀት ዕቅድ ያፀድቃል፣

**16.4** በዞኑ ውስጥ የፓርቲውን ወቅታዊ ችግሮችና ፍላጎቶችን በማጥናት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደረጋል፣

**16.5** የፓርቲው ፕሮግራም፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና የበላይ አካላት ውሳኔዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

**16.6** በዞኑ ሥር በሚካሄዱ የምርጫ እንቅስቃሴዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

**16.7** ከብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 17፡ የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፣**

የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዞኑ ምክር ቤት የሚመረጡ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

**17.1** ሰብሳቢ፣

**17.2** ም/ሰብሳቢ፣

**17.3** ፀሐፊ፣

**17.4** የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

**17.5** የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣

**17.6** የማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ፣

**17.7** የገንዘብና ንብረት ጉዳይ ኃላፊ፣

**17.8** የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣

**17.9** የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ፣

**17.10** የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ፣

**አንቀጽ 18፡ የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣**

የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞኑ ምክር ቤት ሆኖ፣

**18.1** ከፓርቲው መመሪያና ውሳኔዎች በተጨማሪ የዞኑን ምክር ቤት ውሳኔዎች በሥራ ላይ ያውላል፣

**18.2** በዞኑ ውስጥ የፓርቲውን ዓላማዎች ለማስፈፀም የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

18.3 የዞኑን የሥራና የበጀት እቅድ ያዘጋጃል፣ ለዞኑ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፣ ከፀደቀ በኋላም በሥራ ላይ ያውላል::

18.4 በዞኑ ሥር የሚካሄዱ የምርጫ እንቅስቃሴዎችን በበላይነት ያስተባብራል::

18.5 ስለ ሥራ እንቅስቃሴው ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል::

18.6 እንደ አስፈላጊነቱ ከሥልጣኑ ከፊሉን ላቋቋማቸው ኮሚቴዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

18.7 ከዞኑ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 19. የዞን ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ፤

ብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዞን ደረጃ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊያዋቅር ይችላል:: ይህም መዋቅር የሚያገለግለው አስፈላጊ ሁኔታዎች ተሟልተው በአንድ አካባቢ የፓርቲው የዞን ምክር ቤት እና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እስከሚቋቋሙ ድረስ ብቻ ሲሆን፣ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

19.1 ሰብሳቢ፣

19.2 ምክትል ሰብሳቢ፣

19.3 ፀሐፊ፣

19.4 የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

19.5 የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣

19.6 የገንዘብና ንብረት ጉዳይ ኃላፊ፣

19.7 የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ::

## አንቀጽ 20. የዞን ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባር፤

የዞን ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ ኃላፊነትና ተግባሩም በብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

## አንቀጽ 21 የወረዳ ምክር ቤት፣

ተጠሪነቱ እንደየሁኔታው ለዞኑ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይንም ለዞኑ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነው:: የወረዳ ምክር ቤት አባላት ቁጥር በፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ከየመሠረታዊ ድርጅቶች የተወከሉ አባላትን፣ የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የሚያካትት ሲሆን ቀጥሎ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል:-

21.1 ከወረዳው ምክር ቤት አባላት ውስጥ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፣ ይሽራል፣

21.2 የፓርቲውን ዓላማዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣

21.3 የወረዳውን በጀት ያጸድቃል፣

21.4 በወረዳው ምክር ቤት የጸደቁና በወረዳው የሥልጣን ክልል ውስጥ ያሉ የሥራ እቅዶች መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

21.5 ፓርቲው በሚያወጣው የምርጫ ጉዳዮች መመሪያ መሠረት ወረዳውን ወክለው ለፌዴራልና ለክልል ምክር ቤቶች በምርጫ የሚወዳደሩ ዕጩዎች በወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተመልምለው ሲቀርቡለት በመመሪያው መሠረት ተግባሩ መፈፀሙን አረጋግጦ ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲላክ ያደርጋል::

21.6 ለወረዳና ለቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤቶች አባልነት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን ዝርዝር ተመልክቶ ያጸድቃል፣

21.7 እንደየ ሁኔታው ከዞኑ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይንም ከዞኑ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

21.8 የወረዳ ም/ቤት የሥራ ዘመን ሦስት አመት ይሆናል::

**አንቀጽ 22 የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤**

የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በወረዳው ምክር ቤት የሚመረጡ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል::

22.1 ሰብሳቢ፣

22.2 ምክትል ሰብሳቢ፣

22.3 ፀሐፊ፣

22.4 የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

22.5 የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ፣

22.6 የገንዘብና ንብረት ጉዳይ ኃላፊ፣

22.7 የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ፣

22.8 የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣

22.9 የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ::

**አንቀጽ 23. የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፤**

የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለመረጠው የወረዳ ምክር ቤት ሆኖ፣

23.1 የፓርቲውን ፕሮግራም፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም የወረዳ ምክር ቤትና የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች በሥራ ላይ ያውላል::

23.2 ልዩ ልዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

23.3 ስለ ሥራው እንቅስቃሴ በወረዳው ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ወቅት ሪፖርት ያቀርባል፣

23.4 የወረዳ ምክር ቤቱ በማይሰበሰብበት ወቅት በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ የወረዳ ምክር ቤቱ ሲሰበሰብም አቅርቦ ያጸድቃል፣

23.5 የወረዳ ም/ቤቱን መደበኛ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፣

23.6 ወረዳውን በመወከል ለፌዴራልና ለክልል ምክር ቤቶች በምርጫ የሚወዳደሩ ዕጩዎችን መልምሎ በወረዳው ም/ቤት በማስፀደቅ ዝርዝራቸውን ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይልካል፣

23.7 ብሔራዊ ምክር ቤቱ የገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀምን በሚመለከት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከወረዳው የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይልካል፣

23.8 በወረዳው ያለውን የህዝብ ፍላጎትና ችግር በማጥናት ለዞኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያሳውቃል::

23.9 የወረዳ ም/ቤቱን በመወከል ከፓርቲው የበላይ አካላት መመሪያዎችን ይቀበላል፣ አስፈላጊ መረጃዎችንም በተዋረድ ያስተላልፋል፣

23.10 ከወረዳ ምክር ቤትና ከብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

23.11 የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሥራ ዘመን የወረዳ ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል::

አንቀጽ 24. መሠረታዊ ድርጅት (የመኖሪያ የሥራና የትምህርት አካባቢ)

24.1 መሠረታዊ ድርጅት የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በወረዳ ምክር ቤት አማካኝነት ይቋቋማል::

24.2 መሠረታዊ ድርጅቱ ከጠቅላላው መሠረታዊ ድርጅት አባሎች መካከል የተመረጡ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይኖሩታል::

አንቀጽ 25. የመሠረታዊ ድርጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፤

የመሠረታዊ ድርጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለመሠረታዊ ድርጅቱና ለወረዳ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ፣

25.1 አዳዲስ አባላትን ይመለምላል፣ ያደራጃል፣ ይቀሰቅሳል፣

25.2 የፓርቲውን ፕሮግራም ያስተዋውቃል፣

25.3 ከአባሎች መዋጮዎችን እየሰበሰበ ለበላይ አካል ያስረክባል፣

25.4 በበላይ አካል የሚሰጠውን ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፣

25.5 አባሎችን በተመለከተ ልዩ ልዩ መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን ማህደር ያዘጋጃል፣ በበላይ አካል ሲጠየቅም መረጃዎችን ያስተላልፋል፣

25.6 ከወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

**አንቀጽ 26. የፓርቲው አመራር አካላት አመራረጥ፤**

በፓርቲው ውስጥ በማናቸውም ደረጃ ላይ የአመራር አካላት ምርጫ አንድ አባል አንድ ድምጽ በሚለው መርህ መሠረት ምርጫው በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ የሚከናወን ሆኖ:-

**26.1** የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት አባላት አመራረጥ፣

**26.1.1** በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰየመው አስመራጭ ኮሚቴ በብሔራዊ ምክር ቤት የሚቀርቡትንና ከጠቅላላው ጉባዔ የሚጠቆሙ ዕጩዎችን ዝርዝር ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፣

**26.1.2** ስለዕጩ አባላቱ ገለፃ በመስጠት ድጋፍና ተቃውሞ ይጠይቃል፣

**26.1.3** ከፍተኛ ተቃውሞ የቀረበበት እጩ በፈቃዱ ራሱን ካላገለለ ድምጽ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

**26.2** የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት ከላይ በአንቀጽ 26 በተገለፀው ሥነ ሥርዓት መሠረት ይመረጣሉ::

**አንቀጽ 27. ስብሰባና ውሳኔ አሰጣጥ፤**

**27.1** ጠቅላላ ጉባዔ:-

**27.1.1** መደበኛ ጉባኤው በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ ይሆናል:: ሆኖም ብሔራዊ ምክር ቤቱ ሲወስን ወይም ከጉባኤው አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ ልዩ ወይም አስቸኳይ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል:: ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በደንቡ መሠረት ጉባኤ መጥራት የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ብሔራዊ ምክር ቤቱ የጉባዔውን ጊዜ እስከ 6 ወራት ሊያራዝመው ይችላል::

**27.1.2** ጉባዔወ ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል::

**27.2 የብሔራዊ ምክር ቤት ስብሰባ:-**

**27.2.1** የብሔራዊ ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሆናል::
ሆኖም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲወስን ወይም ከብሔራዊ ምክር ቤቱ አባሎች 1/3ኛ ው ሲጠይቁ የምክር ቤቱ ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል:: የብሔራዊ ም/ቤቱ ተለዋጭ አባላት በማንኛውም የም/ቤቱ ስብሰባ ላይ ድምጽ አልባ ተሳትፎ ይኖራቸዋል:: የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላትም በብሔራዊ ም/ቤቱ ስብሰባ ላይ ያለድምጽ ሊሳተፉ ይችላሉ::

**27.2.2** የብሔራዊ ምክር ቤቱ ስብሰባ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል::

27.3 የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ፡-

የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መደበኛ የስብሰባ ጊዜ በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም ሊቀመንበሩ ሲወስን ወይም ከኮሚቴው አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የኮሚቴው ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

27.4 የዞን ምክር ቤት ስብሰባ፡-

27.4.1 የዞን ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ በአንድ አመት አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲወስን ወይም ከምክር ቤቱ አባላት 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የምክር ቤቱ ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

27.4.2 የዞን ምክር ቤቱ ስብሰባ የዞን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል፣

27.6 የዞን አስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባ፡-

የዞን አስተባባሪ ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜ በመደበኛነት በወር አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም ሰብሳቢው ወይም ከኮሚቴው አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የምክር ቤቱ ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

27.7 የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ ፡-

27.7.1 የወረዳ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ በ3 ወር አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲጠይቅ ወይም ከምክር ቤቱ አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የምክር ቤቱ ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

27.7.2 የወረዳ ምክር ቤቱ ስብሰባ የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል፡፡

27.8 የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ፡-

የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ጊዜ በመደበኛነት በወር አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም ሰብሳቢው ሲወስን ወይም ከኮሚቴው አባሎች 1/3ኛው ሲጠይቁ የኮሚቴው ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡

አንቀጽ 28. የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ፤

28.1 በዚህ ደንብ ማንኛውም የፓርቲው ስብሰባ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፣

28.2 የአንድ ስብሰባ ምልዐተ ጉባኤ ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ሊሟላ ካልቻለ ሰብሰባው ለሦስተኛ ጊዜ ተጠርቶ በተገኙት አባላት ይካሄዳል፣

28.3 የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም የሚመለከቱ ጉዳዮች በ2/3ኛ ድምጽ የሚጸድቁ ሲሆን በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚያልፉት ግን በስብሰባው ከተገኙት ከግማሽ በላይ በሚሆኑ አባላት ሲደገፉ ነው፣

28.4 በፓርቲው ስብሰባዎች ላይ የውሳኔ ድምጽ በሚሠጥበት ጊዜ እኩል ድምጽ ከመጣ ሊቀመንበሩ (ሰብሳቢው) ያለበት ወገን ውሳኔ ተቀባይነት ያገኛል፣

28.5 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተሰብሳቢው ውሣኔ መሠረት ሚስጥራዊ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ሊካሄድ ይችላል፣

28.6 ብሔራዊ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በስብሰባ ከተገኙ የምክር ቤቱ አባላት በ2/3ኛ ድምጽ ከተደገፈ በአንቀጽ 28.3 ከተመለከተው የተለየ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሊከተል ይችላል።

## ክፍል ሦስት
## የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

**አንቀጽ 29. ሊቀመንበር፤**

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ፣

29.1 ፓርቲውን በሕጋዊ ሰውነት ይወክላል፣

29.2 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች ይመራል፣

29.3 የፓርቲው ፕሮግራም፣ ደንቦች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

29.4 በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ መሠረት ፓርቲውን በመወከል ልዑካን ይመራል፣ ወይም ሌሎችን ይወክላል፣

29.5 በፓርቲው የገንዘብና የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት የገንዘብ ወጪዎችን በፊርማው ያዛል፣

29.6 በብሔራዊ ምክር ቤቱና በብሔራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የሚወጡ ደብዳቤዎችና ሰነዶች ላይ ይፈርማል፣

29.7 በብሔራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስር የሚቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎችን የዕለት ከዕለት ተግባራት ይከታተላል፣

29.8 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**አንቀጽ 30. ምክትል ሊቀመንበርና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፡-**

ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

30.1 በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የፓርቲው መዋቅር የሚዘረጋበትን ሁኔታ አጥንቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፣ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

30.2 የፓርቲውን አደራጆች በአግባቡ ማሰማራት፣ መከታተልና መቆጣጠር የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲፀድቅም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

30.3 እንደ አመቺነቱ ሀገሪቱን በቀጠናዎች በመከፋፈል የቀጠና ተጠሪዎችን መድቦ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

30.4 የአባሎችን ደህንነትና የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችሉ መዋቅሮችን ይዘረጋል፣

30.5 የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

30.6 ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ወይም መሥራት በማይችልበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፣

30.7 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 31፡ ምክትል ሊቀመንበርና የውጪ ጉዳይ ኃላፊ፤**

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፡-

31.1 ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኙ አባላትን፣ ተባባሪ አባላትንና ደጋፊዎችን ጉዳይ ይከታተላል፣ በሚገኙባቸው አካባቢዎች እንዲደራጁ ያደርጋል፣ እንቅስቃሴአቸውንም ይከታተላል፡፡

31.2 ከተለያዩ መንግሥታት፣ አለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የፓርቲውን አላማ ያስተዋውቃል፣

31.3 ከሌሎች አገሮች አቻ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እንዲመሠረትና የልምድ ልውውጥ መድረኮች እንዲዘጋጁ ጥረት ያደርጋል፣

31.4 የውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

31.5 ሊቀመንበሩና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው (ም/ሊቀመንበር) በማይኖሩበት ጊዜ የሊቀመንበሩን ቦታ ተክቶ ይሠራል፣

31.6 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

**አንቀጽ፡ 32 ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፤**

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

32.1 የፓርቲውን የፕሬስ መግለጫዎች፣ የፕሬስ ኮንፈረንሶች፣ አውደ ጥናቶችና ህዝባዊ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል፤ ያስተባብራል፣ ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጋር በመመካከር መግለጫ የሚሠጡ የአመራር አባላት እንዲመደቡ ያደርጋል፣

32.2 የቅስቀሳ ጽሁፎች፣ ጋዜጦች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ወዘተ እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደ ርጋል፣

32.3 ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳን የሚመለከቱ ስራዎችን ያቅዳል፣ በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚ ቴው ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

32.4 ፓርቲው የሚያከናውናቸውን ልዩ ልዩ ተግባሮች ለሕዝብ ያሳውቃል፣ የፓርቲው ቃል አቀባይ በመሆን ያገለግላል፣

32.5 የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

32.6 ሊቀመንበሩና ሁለቱ ም/ሊቃነመናብርት በማይኖሩበት ጊዜ የሊቀመንበሩን ቦታ ተክቶ ይሠራል::

32.7 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 33. ምክትል ሊቀመንበርና የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ:-

ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

33.1 የፓርቲውን የገቢ ምንጭ ያፈላልጋል፣ የገቢ ማስገኛ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፣

33.2 የፓርቲውን የገቢና የወጪ ዝርዝር የያዘ ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ በየበጀት ዓመቱ አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በማቅረብ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

33.3 የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በትክክል እንዲጠበቅና በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል ያደ ርጋል የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የፓርቲው ሂሳብ አያያዝ በሕግ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አሠራርን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣

33.4 በየወቅቱ አስፈላጊ የሆኑ የሂሳብ መግለጫዎች በማዘጋጀት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፣ በየበጀት ዓመቱ የፓርቲውን ገቢና ወጪ ዝርዝር የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ በማዘጋጀትም ለኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን በማቅረብ ያስመረምራል፣

33.5 የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

33.6 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል::

## አንቀጽ 34: ዋና ፀሐፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

34.1 የፓርቲውን ዋና ጽ/ቤት ያደራጃል፣ በኃላፊነት ይመራል፣ ሌሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም እንዲደራጁ ያደርጋል፣

34.2 የፓርቲውን ዋና ጽ/ቤት ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ የቋሚ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደርን የሚመለከት መመሪያም ያዘጋጃል፣ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚተው ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

34.3 የጽህፈት ቤቱን የደብዳቤ ልውውጦች ያከናውናል፣ የጽህፈት ቤቱ ሰነዶችና ማህተም ሁሉ በስርዓት መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፣

34.4 የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ቃለ ጉባኤዎች ይይዛል፣

34.5 ብሔራዊ ም/ቤቱ በሚያወጣው የገንዘብ አጠቃቀም መመሪያ መሠረት የገንዘብ ወጭዎችን በፊርማው ያዛል፣

34.6 ስለፕሮቶኮል ጉዳዮች ዝርዝር የአፈጻጸም ስልቶችን በማዘጋጀት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲጸድቅ በሥራ ላይ ያውላል፣

34.7 ስለጽህፈት ቤቱ የሥራ እንቅስቀሴ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፣

34.8 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 35፡ ምክትል ፀሐፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለዋና ፀሐፊው ሆኖ ፡-

35.1 የጽ/ቤቱን ሠራተኞች የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

35.2 ዋና ፀሐፊውን በሥራ ያግዛል፣

35.3 ዋና ፀሐፊው በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሠራል፣

35.4 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከዋና ፀሐፊው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 36፡ የጥናትና ምርምር ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

36.1 ለፓርቲው ሥራ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል ፣

36.2 በፓርቲው ርዕዮተ ዓለምና ፖሊሲዎች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ሰነዶችን ያዘጋጃል፡፡

36.3 የፓርቲው አባሎች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል የተለያዩ የሥልጠናና የአቅም ግንባታ ስልቶችን ይቀይሳል፣ በሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴው ሲፈቀዱም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

36.4 የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

36.5 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 37 ፡ የሕግና ሥነ-ሥርዓት ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

37.1 ፓርቲውን በመወከል ወይንም ጠበቃ በመቅጠር በማንኛውም ፍ/ቤት ወይም መንግሥታዊ አካል ፊት ክስ ይመሰርታል፣ ይከላከላል፣ ይከራከራል፣ ይግባኝ ያቀርባል፣ እንዲሁም የፍርድ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

37.2 የፓርቲው አባላት መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ብሔራዊ ም/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሥነ- ሥርዓት ጉዳዮችን ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሠጣል፣

37.3 አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ለተለያዩ የፓርቲ አካላትና አባላት ከፓርቲው ሥራ ጋር በተየያዘ የሕግ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣

37.4 ፓርቲውን በሚመለከት በማንኛውም የሕግ ጉዳይ ላይ ኃላፊ ሆኖ ይሰራል፣ በፓርቲው ሠነዶችም ላይ የሕግ አስተያየት ይሠጣል፣

37.5 የሕግና ሥነ-ሥርዓት ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

37.6 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 38. የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

38.1 በፌዴራል፣ በክልልና በአካባቢ ም/ቤቶች ፓርቲውን ወክለው ለምርጫ የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መመዘኛ፣ ብዛትና የሥራ መመሪያ በማዘጋጀት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚመለከተው አካል ተመዝግበው ተገቢውን ማስረጃ ማግኘታቸውንም ያረጋግጣል፣

38.2 የምርጫው ጊዜ ከመድረሱ በፊት የፓርቲውን የምርጫ ማኒፌስቶ ለፓርቲው አባላት ደጋፊዎችና ለሕዝብ እንዲሰራጭ ያደርጋል፣ በየደረጃው የሚገኙ አባላትም በምርጫው ዙሪያ በቂ ስልጠናና ትምህርት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣

38.3 የፓርቲውን የምርጫ ታዛቢዎች/ወኪሎች መመዘኛ፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ ብዛት፣ አመዳደብና የስነ- ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲጸድቅ እንዲሠራጭ ያደርጋል፣

38.4 በየደረጃው በሚገኙ ም/ቤቶች ፓርቲውን ወክለው የሚሳተፉ አባላት የም/ቤት ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወናቸውንና ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በየጊዜው መገናኘታቸውን ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛም ያደርጋል፣

38.5 ከምርጫና ከተመራጮች እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው የመንግሥትና ሌሎች አካላት ጋር ይነጋገራል፣ ስለ ሁኔታው ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ሪፖረት ያቀርባል፣

38.6 የምርጫ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

38.7 ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 39 የዕቅድና ስትራቴጅ ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ:-

39.1 የፓርቲውን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ፣ ስልትና ስትራቴጅ በማዘጋጀት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እንዲፀድቅ ያደርጋል፣ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፣

39.2 በፓርቲው እንቅስቃሴና የትግል ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን በመለየትና በክብደታቸውም ቅደም ተከተል በማስቀመጥ የተለያዩ ስልቶችና አቅጣጫዎችን ይቀይሳል፣

39.3 የተለያዩ አለማቀፋዊ፣ አካባቢያዊና አገራዊ ሁኔታዎችንና የኃይል አሰላለፎችን በመገምገም በፓርቲው እንቅስቃሴና የትግል ውጤት ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን እንደምታ ይተነትናል፣

39.4 ፓርቲው ራሱን በገንዘብ፣ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ የሚያጠናክርበትን እንዲሁም የትግል አድማሱን ማስፋት የሚችልበትን ስልትና ስትራቴጅ ይቀይሳል፣

39.5 የዕቅድና ስትራቴጂ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

39.6 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 40: የማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

40.1 በአባላት መካከል የመቀራረብና የአንድነት መንፈስን የሚያጠናክሩ ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ የልምድ ልውውጥ መድረኮችንም ያመቻቻል፣

40.2 የፓርቲውን የባህልና የኪነት ቡድኖች ያቋቁማል፤ ይመራል፤ ፓርቲው መዋቅሩን በዘረጋባቸው አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ዝግጅቶቻቸውን እንዲያቀርቡም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

40.3 የአካል ጉደተኞችና ከኤች. አይ. ቪ /ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወገኖች በፓርቲው ውስጥ ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፣

40.4 አባላት ከትግሉ ጋር በተያያዘ የሚደርሱባቸው ማህበራዊ ችግሮች እንዲወገዱ ጥረት ያደርጋል፣

40.5 የማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፣

40.6 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 41 የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

41.1 ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ባህላዊ መስኮች የላቀ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ፤ የሚያስችል የሥርዐተ-ፆታ ፖሊሲ ያዘጋጃል፣

41.2 ሴቶች መብቶቻቸውን ለማስከበር በማህበር እንዲደራጁ ያበረታታል፣ በጉዳዩ ዙሪያ ከሚሰሩ ማህበራት ጋር ፓርቲው የሚተባበርበትንና የሚተጋገዝበትን መንገድ ይፈልጋል፣

41.3 የፓርቲው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ መሆኑን ይከታተላል፣ የፓርቲው አባላት ስለ ሥርዓተ-ፆታ ያላቸው ግንዛቤ የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል::

41.4 የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል::

41.5 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 42. የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሆኖ፣

42.1 ወጣቶች በፓርቲው ውስጥ የነቃና ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይጥራል፡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

42.2 ወጣቱ ከጎጂ ባህሎችና ልማዶች ርቆ አገራዊ ራዕይና መልካም ሥነ-ምግባር እንዲኖረው የሚረዱ ስልቶችን ይቀይሳል::

42.3 ወጣቶች እንዲደራጁ ያግዛል፣ ፓርቲው ከወጣት ማህበሮች ጋር የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖረው ይጥራል::

42.4 የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል::

42.5 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 43፡ ምክትል የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለድርጅት ጉዳይ ኃላፊ (ምክትል ሊቀመንበር) ሆኖ፡-

43.1 ምክትል ሊቀመንበርና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ በሌለበት እሱን ተክቶ ይሠራል::

43.2 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና ከድርጅት ጉዳይ ኃላፊው (ምክትል ሊቀመንበር) የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 44፡ ምክትል የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለውጭ ጉዳይ ኃላፊ (ምክትል ሊቀመንበር) ሆኖ

44.1 ምክትል ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ በሌለበት እሱን ተክቶ ይሠራል::

44.2 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና የውጭ ጉዳይ ኃላፊው (ምክትል ሊቀመንበር) የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

## አንቀጽ 45፡ ምክትል የህዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሕዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ (ምክትል ሊቀመንበር) ሆኖ፡-

45.1 ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ በሌለበት እሱን ተክቶ ይሠራል::

45.2 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሕዝብ ግንኙት ጉዳይ ኃላፊው (ምክትል ሊቀመንበር) የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 46፡ ምክትል የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ፤

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ (ምክትል ሊቀመንበር) ሆኖ

46.1 ምክትል ሊቀመንበርና የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ በሌለበት እሱን ተክቶ ይሠራል፡፡

46.2 ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊው (ምክትል ሊቀመንበር) የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ አካላት

አንቀት 47. የሕዝብ ተመራጮች፤

በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ/ ክፍለ ከተማና ቀበሌ ምክር ቤቶች ፓርቲውን ወክለው የሚሳተፉ የሕዝብ ተመራጮች የየራሳቸውን ተጠሪዎች የሚሰይሙ ሲሆን ከፓርቲው እና ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር የሚኖራቸው የሥራ ግንኙነትና አሠራር ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 48. የአማካሪዎች ሸንጎ፤

በብሔራዊ ምክር ቤት የሚመረጡ በዕውቀታቸው፣ በሥራ ልምዳቸው፣ በዕድሜአቸውና ከህብረተሰቡ ጋር ባላቸው ቅርብ ትስስር፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖትና እንደ አግባቡ የነባር ባህላዊ ተቋማት መሪዎችን የሚያካትት እና ያታዊ ተዋጽኦን የጠበቀ የአማካሪዎች ሸንጎ ይቋቋማል፣ ዝርዝሩ ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 49. የኢዲቶሪያል ቦርድ፤

49.1 ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ምክር ቤት የሆነና ሰባት አባላት ያሉት የፓርቲውን መገናኛ ብዙሃን የሚመራ ኢዲቶሪያል ቦርድ በብሔራዊ ምክር ቤቱ ይቋቋማል፡፡

49.2 የኢዲቶሪያል ቦርዱ አባላት በብሔራዊ ምክር ቤቱ ይመረጣሉ፡፡ የሥራ ዘመናቸውም ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡

49.3 የኢዲቶሪያል ቦርዱ የፓርቲውን ልሣን ያዘጋጃል፡፡ የራሱን የኢዲቶሪያል ፖሊሲና የሥራ መመሪያም አዘጋጅቶ በብሔራዊ ምክር ቤት ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 50. የገንዘብና ንብረት አጠቃቀም፤**

**50.1** ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚሰበሰቡትን ማንኛውንም ገንዘብ ብሔራዊ ም/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ይልካሉ፡፡

**50.2** ቅ/ጽ/ቤቶች የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት በሚመድብላቸው በጀት ይንቀሳቀሳሉ፡፡

**50.3** ማንኛውም የገንዘብና የንብረት አጠቃቀም ብሔራዊ ምክር ቤቱ የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 51. የሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ፤**

**51.1** የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ የሚጥስ፣ የአባልነት ግዴታውን የማይወጣና ፓርቲውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ተግባራትን ሲፈጽም የተገኘ አባልና የአመራር አካል ብሔራዊ ም/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የስነ ስርዓት እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፣

**51.2** የአንቀጽ 12.5 እና 37.2 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በየደረጃው በሚገኙ የአመራር አባላት ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ የሚፀናው አባላቱ አባል በሆኑበት አካል 2/3ኛ ድምጽ ሲፀድቅ ነው፣

**51.3** በማንኛውም የፓርቲው እርከን አንድን አባል ከአባልነት ለማስወገድ ውሳኔውን በሚ ሰጠው አካል በ2/3ኛ ድምጽ መወሰን አለበት፣

**51.4** እርምጃ የተወሰደበት አባል ወይም አካል ወይም ክሱ ውድቅ የተደረገበት አባል ወይም አካል ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው፣

**51.5** የሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ ዝርዝር መመሪያ በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ በብሔራዊ ምክር ቤቱ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**አንቀጽ 52. ስለደንብ መሻሻል፤**

ይህ ደንብ ሊሻሻል የሚችለው ከጠቅላላ ጉባዔ አባላት ቢያንስ 1/3ኛ የሚሆኑት ጥያቄ ሲያቀርቡ ወይም የማሻሻያ ጥያቄው በስብሰባ ላይ ከተገኙት የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት ከግማሽ በላይ ድጋፍ ሲያገኝና በጥያቄው መሠረት ጠቅላላ ጉባዔው በ2/3ኛ ድምጽ ሲወስን ነው፡፡

**አንቀጽ 53. ስለፓርቲው መፍረስ፤**

ፓርቲው ሊፈርስ የሚችለው የመፍረስ ጥያቄው በብሔራዊ ምክር ቤቱ 2/3ኛ ድምጽ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው 1/2ኛ አባላት ሲቀርብና የመፍረስ ጥያቄው በጠቅላላ ጉባኤው አባላት በ2/3ኛ ድምጽ ሲደገፍ ነው፡፡

**አንቀጽ 54. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ፤**

ይህ ደንብ ከሰኔ 11 /2000 ዓም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡